# ህም!

አንተም ሰው ሆንክና
እንደ ሰው ቆምክና
ባለህ ሁለመና
ትንጎራደዳለህ በሙሉ ቁመና…

ልቤ እያዘነብህ
አንጀቴ ሲያርርብህ
እጄ ሳያርፍብህ
ደንድኖ ትዕቢተኛው ልብህ…

ጉድህ እንዲወጣ
ቀውጢ ቀን በመጣ
አንተን የሚቀጣ
መከራ፣ ጣጣና፣ ፈንጣጣ…

ዕለታቱ ያልፋል
ውሃውም ይጐርፋል
የሞተውም ያርፋል
ለመቸውም ትዝብቱ ይተርፋል!

ገ/ኢ. ጐርፉ።